በስደት ላይ ያለው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE
ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
PATRIARCHATE HEAD OFFICE IN EXILE

ቀን: 04/02/07 ዓ.ም
Date: 09/15/14
ቁጥር: 090/2007
Ref. No: 090/2014

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"ዮሐ3:16

# ለሚመለከተው ሁሉ፤

ጉዳዩ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ መርቆሬዎስን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት መታሰቢያና በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የተገዛውን የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ቀን መተላለፍ ማሳወቅን ይመለከታል፤

በሕጋዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስነታቸው ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን መዓርግ የበቁበትን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና በቅርቡ በሜሪ ላንድ እስቴት የገዛውን አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ ምረቃ በዓል ቅዳሜ ኅዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም (Saturday, November 22,2014)ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኑን በመግለጽ ለአብያተ ክርስቲያናት ጥሪ ማስተላለፉ ይታወቃል።

ሆኖም ቋሚ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥቅምት 4ቀን 2007 ዓ. ም.(October 14, 2014) በአደረገው ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ የዝግጅቱን ይዘት በተመለከተ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ ሰፊ ውይይት ከአደረገ በኋላ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ሊደረግ የታሰበው የበዓል ዝግጅት በሚከተሉት ምክንያቶች ለጊዜው ተላልፎ በግንቦት ወር ከሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ዓመታዊ ስብሰባ ጋር ተያይዞ እንዲከበር ውሳኔ አስተላልፎአል።

1. ለዚህ ታሪካዊና ዓለም አቀፍ በዓል የታሰበው ቅድመ ዝግጅት በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ሊሟላ ስለአልቻለና በቂ የዝግጅት ጊዜ ስለሌለ፤
2. በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ከቅዱስነታቸው 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ጋር የተቀራረበ በመሆኑ በርካታ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት በበዓሉ ላይ መገኘት የማትሉ መሆናቸውን ስለታወቀ፤
3. በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በኅዳር ወር የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል የመታሰቢያ በዓል ኅዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም.(November 22, 2014) የሚከበር በመሆኑ፤
4. በግንቦት ወር አዲስ በተገዛው የመንበረ ፓትርያክ ጽ/ቤት ከሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ(ርክበ ካህናት )ዓመታዊ ስብሰባ ጋር ይህን ታላቅና ታሪካዊ በዓል በአንድ ላይ ለማክበር በቂ የዝግጅት ጊዜ ስለሚሰጥና ሁሉም ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ለማድረግ አመች በመሆኑ፤

ስለዚህ ከዚህ በላይ በዋናነት የተጠቀሱትንና ሌሎችን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅዱስነታቸው 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና ቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ የገዛው አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ቅዳሜ ኅዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም(Saturday, November 22, 2014)እንዲከበር የተወሰነው ለጊዜው እንዲተላለፍና በግንቦት ወር 2007 ዓ.ም በተሻለ ዝግጅት እንዲከበር በቋሚ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ የተወሰነ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር፤

ቆሞስ አባ ጽጌድንግል ደገፋው
የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ
Komos Abba Tsigedengel Degefaw
General Manager of the Patriarchate Head Office

ግልባጭ፤
ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጽ/ቤት፤
ለመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፤
ለቋሚ ሲኖዶስ አባላት በየአሉበት፤